*የመ/ቁ 268784*

*ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም*

*ዳኛ፡- ሀዲስ ነቃጥበብ*

*ከሣሽ፡- አባ ዳንኤል መልከፀዲቅ ሀብተማሪያም*

*ተከሣሽ፡- አቶ ይማም ሁሴን ቡሽራ*

*መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡*

# ፍርድ

ከሣሽ በአጭር ስነ-ስርዓት ታይቶ እንዲወሠን በ27/02/02011 ዓ.ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ በከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል በቀን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ በ10/04/2004 ዓ.ም በተደረገ የገንዘብ ብድር ውል ስምምነት ተከሳሽ ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ተበድረው የወሠዱ ሲሆን ይህን በብድር የወሠዱትን በ1 ወር ውስጥ ለመመለስ የተስማሙ መሆኑን በ10/04/2004 ዓ.ም በተደረገ የመንደር ብድር ዉል ዋስትናም በተከሳሽ ስም በን/ስ/ላ/ክ/ከ ጀሞ ሳይት የቤቱ አይነት ስቱዲዮ ህንፃ ቁጥር 43 የቤት ቁጥር JG-B43/24 የሆነውን የጋራ መኖሪያ ቤት ካርታን ጨምሮ ቤቱን የተመለከቱ ሰነዶችን ከመረከብ ባሻገር ቤቱን ይዘው ያሉ መሆኑን ተከሳሽ በተባለው ጊዜ ገንዘቡን መመለስ ባይችሉ ቤቱን በእዳ ማቻቻያነት ስመ ሀብቱን ወደ ከሳሽ ለማዞር እንደተስማሙ የተበደሩትን ገንዘብም እንዳልከፈሉ ከሳሽ ከተከሳሽ በተሰጣቸው ውክልና መሰረትም ለኮንዶሚኒየም ቤት ቅድመ ክፍያ ብር 5,434 ፡ የካርታና የእዳ እገዳ ብር 600 ፡ የአገልግሎት ብር 10 ፡ ከኢ/ት ንግድ ባንክ ለተበደሩት ማሰረዣ ብር 200 ፡ ለካርታ ማረጋገጥና ማህደር ማጣሪያ ብር 200 በድምሩ ብር 6,444 እንደከፈሉ፡፡ ተከሳሽ በብድር ውሉ መሠረት ተበድረው የወሠዱትን ገንዘብና ከብድር ዉሉ ጋር በተያያዘ የወጣውን ወጪ ድምር ብር 256,444 ያልከፈሉ በመሆኑ ከነወለዱ እንዲሁም በክሱ ምክንያት የወጣውን ወጪ ጭምር ይወሠንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ በማስረጃነትም የሰነድና የሰው ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡

ተከሳሽ ፍ/ቤቱ እንዲከላከሉ በፈቀደላቸው መሰረት በጥር 29 ቀን 2011 ዓ.ም በተፃፈ ባቀረቡት መልስ ተከሳሽ በአዋዋይ ፊት የተበደሩት ገንዘብ ብር 70,000 መሆኑንና

ከብድሩ እለት ከ10/04/2004 በኋላ ገንዘቡን ለተከሳሽ ለመስጠት ቢፈልጉም ከሳሽን ለማግኘት እንዳልቻሉ ተከሳሽ ቤቱን ላለፉት ሰባት አመታት በማከራየት 3,000 252,000 በመሆኑ የብድር ገንዘቡ ክፍያ ከኪራይ ገንዘቡ የተሰበሰበ መሆኑን የብር 250,000 የብድር ዉሉን የፈረሙት በወቅቱ በከፍተኛ ሁኔታ በህመም ላይ ይገኙ የነበረ በመሆኑና ከፍተኛ ወጪ የተጠየቁ በመሆኑ በምስክሮች ተፅእኖ መሆኑንና በቅን ልቦና ያልተደረገና በከፍተኛ ስህተትና ተንኮል የተደረገ መሆኑን በመንደር ውል የተደረገውን ውልም ተከሳሽ እንዳልፈረሙ ብር 6,444 እንደከፈላቸው የጠየቁትን ክፍያ የከፈሉት ተከሳሽ እንጂ ከሳሽ ባለመሆናቸው ሊከፍሉ እንደማይገባ ብር 70,000 ለመክፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልፀው የሰነድና የሰው ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር በሰማበት እለት ከሳሽ ተከሳሽ የተበደሩት ብር 250,000 መሆኑን ለከሳሽም ውክልና እንደሰጡ ውል ይፍረስልኝ በማለት ክስ በማቅረብ ያልጠየቁ መሆኑን ብር 6,440 የሆነው ገንዘብ በተከሳሽ ስም የተከፈለ ቢሆንም የከፈሉት ከሳሽ እንደሆኑ የገለፁ ሲሆን ተከሳሽ ባቀረቡት ክርክር በተከሳሽ የቀረበው ማስረጃ የተቀነባበረ መሆኑን የተበደሩት ብር 70,000 እንደሆነ ለባንክ በከሳሽ የተከፈለ ክፍያ እንደሌለ ለከሳሽ የሰጡት ውክልናም የሌለ መሆኑን ገልፀው በፅሁፍ ያቀረቡትን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለከሣሽ ሊከፍሉ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከሣሽ በተከሳሽ ላይ ክስ ያቀረቡት ተከሣሽ ተበድረው የወሠዱትን ገንዘብ በብድር ውሉ መሠረት ያልመለሱ ስለሆነ ተከሳሽ ተበድረው የወሠዱትን ገንዘብ እንዲሁም ከብድር ዉሉ ጋር በተያያዘ የወጣውን ወጪ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ሲሆን ተከሳሽ ባቀረቡት ክርክር ደግሞ የተበደሩት ብር 70,000 መሆኑንና ከብድር ውሉ ጋር በተያያዘ በከሳሽ የወጣ ወጪ የሌለ በመሆኑን ሊከፍሉ እንደማይገባ ገልፀዋል:: ከሳሽ እና ተከሳሽ በ10/04/2004 ዓ.ም በተፃፈ የገንዘብ ብድር ውል ስምምነት ያደረጉ መሆናቸውን፣ በዚህ የብድር ውል መሠረት ተከሳሽ ከከሣሽ በጥር 9 ቀን 2004 ዓ/ም ገንዘቡን ለመክፈል በመስማማት ብር 250,000.00 ተበድረው የወሠዱ መሆናቸውን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ ቀርቧል፡፡

በህጉ የተመለከቱ መስፈርቶችን በማሟላት የተመሰረቱ ውሎች በህግ ፊት የሚፀና ህጋዊ ውጤትን የሚያስከትሉ ሲሆን በተዋዋይ ወገኖች ላይም ህግ መሆናቸውን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1678 እና 1731/1 ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ በተደረገ ውል ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች ደግሞ በየበኩላቸው መፈፀም ያለባቸውን ተግባራት /ግዴታዎች/ በውሉ መሠረት የመፈፀም ግዴታ ያለባቸውን ሲሆን አንደኛው ተዋዋይ ወገን በውሉ መሠረት መፈፀም ያለበትን ተግባር ከፈፀመ እና ሌላኛው ተዋዋይ ወገን መፈፀም ያለበትን ተግባር ሣይፈጽም ከቀረ በውሉ መሠረት የፈፀመው ወገን ውሉን መሠረት በማድረግ ሌላኛው ተዋዋይ ወገን መፈፀም ያለበትን ተግባር እንዲፈጽም መጠየቅ ይችላል ይህም ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1757፣ 1771 እና ሌሎች ድንጋጌዎች መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ መርህ ስለእያንዳንዱ አይነት ውሎች ላይም ተፈፃሚነት አለው፡፡

ግራቀኙ ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉት ውል የብድር ውል ከሆነ ተበዳሪው ወገን በብድር ውሉ መሠረት ተበድሮ የወሠደውን ገንዘብ በብድር ውሉ ላይ የብድር ገንዘቡን መክፈያ ጊዜ ተወስኖ ከተቀመጠ ይህ የመክፈያ ጊዜ ሲደርስ፣ ተበዳሪው ወገን ለአበዳሪው የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡ ተበዳሪው ወገን በዚህ ግዴታው መሠረት ተበድሮ የወሠደውን ገንዘብ ካልመለሰ አበዳሪው ወገን ውሉን እንዲሁም ህጉን መሠረት በማድረግ ተበዳሪው ወገን በብድር የወሠደውን ገንዘብ እንዲመልስለት መጠየቅ ይችላል፡፡ ይህም በፍ/ብ/ህ/ቁ 2482፣ 2483 ስር ተመልክቶ ይገኛል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ከሳሽ እና ተከሳሽ ያደረጉት ውል የብድር ውል ሲሆን በዚህ የብድር ውል ተከሳሽ ከከሣሽ ላይ ብር 250,000.00 ተበድረው የወሠዱ ሲሆን ይህን በብድር የወሠዱትን ገንዘብ በ1 ወር ውስጥ ለመመለስ በመስማማት ግዴታ የገቡ መሆናቸውን ውሉ በግልጽ ያስረዳል፡፡በታህሳስ 10 ቀን 2004 ዓ/ም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የብድር ውል ሁለት ሲሆን እነዚህ ሁለት ተመሳሳይ ውሎች አንደኛው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት ዘንድ የተደረገ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የመንደር ውል ነው፡፡ ተከሳሽ ከከሳሽ የተበደሩት ብር 70,000 መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ቢሆንም ውሎቹ ብር 250,000 የተበደሩ መሆኑን የሚያስረዱ ሲሆን በተለይ አንደኛው በመንግስት አካል ዘንድ የተመዘገበው ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል ውልን ለማዋዋል ስልጣን ባለው በመንግስት አካል ፊት የተደረገ በመሆኑ ተከሳሽ ውሉ በተፅእኖና በተንኮል የተደረገ ነው የተበደርኩትም ብር 70,000 ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የብድር ውሉን ካደረጉበት ጊዜ በኋላም ይህን በመጥቀስ ክስ አቅርበው ውሉ እንዲፈርስ ያደረጉበት

አግባብ የለም፡፡ በዚህም ተከሳሽ ይህን በብድር የወሰዱትን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ይህን ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የከፈሉ መሆኑን በመግለፅም ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ብር 250,000.00 የሆነውን ገንዘብ ለከሳሽ ሊከፍሉ ይገባል፡፡

ከሳሽ ለኮንዶሚኒየም ቤት ቅድመ ክፍያ ብር 5,434 ፣ የካርታና የእዳ እገዳ ብር 600 ፣ የአገልግሎት ብር 10 ፣ ከኢ/ት ንግድ ባንክ ለተበደሩት ማሰረዣ ብር 200 ፣ ለካርታ ማረጋገጥና ማህደር ማጣሪያ ብር 200 በድምሩ ብር 6,444 የከፈሉ መሆኑን ገልፀው ያቀረቡትን መከራከሪያ በተመለከተ ምንም እንኳን ከሳሽ ከተከሳሽ በታህሳስ 10 ቀን 2004 ዓ/ም ውክልና የተሰጣቸው ቢሆንም የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ገንዘቡ የተከፈለ መሆኑን የሚያሳየው በተከሳሽ በራሳቸው ስም እንጂ በውክልና የተከፈለ መሆኑን የማያመለክት ሲሆን ከዚህ አኳያም ከሳሽ ገንዘቡን በተሰጣቸው ውክልና መሰረት የከፈሉ መሆኑን ባላስረዱበት አግባብ ገንዘቡን ተከሳሽ እንዲከፍሉ ያቀረቡት መከራከሪያ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፡፡

## ውሳኔ

1. ተከሳሽ ብር 250,000 (ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ገንዘቡ መከፈል ከነበረበት ከጥር 9 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሠብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈሉ፡፡
2. ከሳሽ ከብድር ዉሉ ጋር በተያያዘ ያወጣሁት ነው በማለት የገለፁትን ብር 6,444 የሆነውን ገንዘብ ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍሉ አይገባም፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ለዳኝነት የተከፈለውን ብር 5,414፣ ለቴምብር ቀረጥ ብር 60 ፣ የጠበቃ አበል በጥብቅና ውሉ መሰረት ብር 15,000 ልዩ ልዩ ወጪዎች በቁርጥ ብር 300 ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈሉ፡፡

## ትዕዛዝ

1. ይግባኝ መብት ነው፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡